ACPS
Alexandria City Public Schools

# የጤና ኢንሹራንስ ምርጫዎች

## ለአሌክሳንድርያ ህጻናት እና ቤተሰቦች

እያንዳንዱ ህጻናት ውድ የሆነውን የዶክተሮች፣ የሆስፒታል፣ የጥርስ ሃኪሞች እና የሌሎች የጤና አገልግሎት አቅራቢዎች ወጪ ለመክፈል የጤና ኢንሹራንስ ያስፈልጋቸዋል። እንደ መኪና ኢንሹራንስ ሁሉ ቤተሰቦች አብዛኛውን ግዜ "ፕሪመየም" የሚባለውን ወራሃዊ ክፍያ ለጤና ኢንሹራንስም ይከፍላሉ። አሰሪዎ የጤና ኢንሹራንስ አገልግሎት ሊሰጠዎት ይችላል ወይም ከግል የጤና ኢንሹራንስ ኩባንያ ሊገዙት ይችላሉ። ስራዎት የጤና ኢንሹራንስ የማይሰጦት ከሆነ ወይም የጤና ኢንሹራንስ ለመግዛት የማይችሉ ከሆነ የተወሰኑ ህጻናት ከመንግስት ያለክፍያ ወይም በቅናሽ የጤና ኢንሹራንስ ሊያገኙ ይችላሉ።

### ለአገልግሎቱ መብቃት

**በርካታ የአሌክሳንድርያ ኢንሹራንስ አልባ ህጻናት ለዚህ ሽፋን ሊበቁ ይችላሉ።** ብዙ ቤተሰቦች ይህንን አገልግሎት ለማግኘት እንዴት ማመልከት እንዳለባችው አያውቁም ወይም ልጆቻቸው ተቀባይነት እንደማያገኙ ይገምታሉ። ጥቂት ቤተሰቦች ኢሚግራንቶች የመንግስትን የጤና ኢንሹራንስ ለማግኘት ማመልከት እንደማይችሉ ያስባሉ። ሌሎች ቤተሰቦች ደግሞ ገቢያቸው እጅግ በዙ ስለሆነ የመንግስትን የጤና ኢንሹራንስ ማግኘት እንደማይችሉ ያምናሉ። ይህ በራሪ ወረቀት ኢንሹራንስ ሽፋን ለማግኘት እንዴት ማመልከት እንዳለቦዎት መረጃ ይሰጠዎታል።

### ማመልከት

በቨርጂኒያ ኮመን ዌልዝ አማካኝነት የጤና ኢንሹራንስን ለማግኘት ማመልከት ያለ ክፍያ ወይም በቅናሽ ዋጋ የምሳ አገልግሎት ለማግኘት ከሚደረገው ማመልከቻ ጋር ተመሳሳይ ነው።

ልክ እንደ ትምህርት ቤቱ የምሳ ፕሮግራም ሁሉ ለመንግስት የጤና ኢንሹራንስ ለመብቃት ቤተሰቦዎ በሚያገኙው ገቢ እና በቤተሰቦዎ አባላት ቁጥር ላይ ይመሰረታል። ህጻናት ለዚህ አገልግሎት ለመብቃት የአሜሪካ ዜግነት ያላቸው ወይም ህጋዊ ኢሚግራንቶች እና የቨርጂኒያ ኗሪ መሆን አለባቸው። አመልካቾች የህጻኑን ሶሻል ሴኩዩሪቲ ቁጥር፣ የአሜሪካ ዜግነትን የሚያረጋግጥ ዶክመንት ወይም ህጋዊ የመኖሪያ ፍቃድ ፣ እና የቨርጂኒያ ኗሪነት ማረጋገጫ። ዜጋ መሆን አያስፈልግም፤ የገቢውን መጠን የሚያሟሉ ህጋዊ ኑዋሪዎች ለዚህ አገልግሎት ብቁ ናቸው። የህጻኑ ቤተሰቦች የኢሚግሬሽን ሁኔታ የሚገልጽ መረጃ አስፈላጊ አይደለም።

### በአሁኑ ሰአት ያሉት የመንግስት ኢንሹራንስ ፕሮግራሞች:

**FAMIS Plus** (Medicaid) ወይም ሜዲኬድ አንዱ ነው። ይህ ኢንሹራንስ አዲስ ከተወለዱ ህጻናት ጀምሮ እድሜቸው 19 ለሚደርሱ ሰዎች ነው። የቤተሰባቸው አባላት ቁጥር አራት የሆኑ እና አመታዊ ገቢያቸው$38,111 የሆኑ አባወራዎች ለዚህ ፕሮግራም ይበቃሉ።

**FAMIS** የተሰኘው ፕርግራም ደግሞ አዲስ ከተወለዱ ህጻናት ጀምሮ እድሜቸው 19 ለሚደርሱ ምንም ኢንሹራንስ ለሌቸው ነው። ይህ ፕሮግራም በ FAMIS Plus. ለመካተት የገቢያቸው ጣሪያ እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ ላልቻሉ አባ ወራዎች ነው። የቤተሰባቸው አባላት ቁጥር አራት የሆኑ እና አመታዊ ገቢያቸው እስከ $52,788 የሚደርሱ ቢሆኑም ልጆችቸው ለFAMIS ሊበቁ ይችላሉ።

### የቨርጂኒያ የጤና ኢንሹራንስ የገበያቦታ/ Virginia Health Insurance Marketplace

የአፎርዴብል ኬር አዋጅ (ኦባማ ኬር በመባል ይታወቃል) ቤተስቦች የግል የጤና ኢንሹራንስ እንዲገዙ ለማገዝ የግል የጤና ኢንሹራንስ ገበያ አቋቁሞል። የ2020 የጤና ገበያው የመጀመሪያ ጊዜ ከኖቬምበር 1 ቀን 2019 ይጀምራል። ለዚህ ብቁ ለመሆን ግለሰቦች እናቤተሰቦች ዜጋ ወይም ህጋዊ ኖሪ እና የስቴቱ ነዋሪ መሆን አለባቸው። ቤተሰቦች ወርሃዊ የኢንሹራን ፕሪሚይርም ክፍያ ይከፍላሉ። ብዙዋች ክፍያውን ለመቀነስ ለድጋፍ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ለበለጠ መረጃ እዚህ ይገኛል: www.healthcare.gov.

### እርዳታ ማግኘት

በሰሜን ቨርጂኒያ የሚኖሩ ዋስትና ያልገቡ ቤተሰቦች በእነዚህ ፕሮግራሞች ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው ነጻና ሚስጥራዊ ድጋፍ በሚከተሉት መ/ቤቶች አማካይነት ማግኘት ይችላሉ፡

**ኢኖቫ አጋርነት ለጤናማ ልጆች (Inova Partnership for Healthier Kids)** በስልክ ቁጥር 703-698-2550 ከሰኞ እስከ አርብ ከ 8:30 ጥዋት-5:00 ከሰዓት በመደወል ማግኘት ይቻላል።

**ኔበርሁድ የጤና አገልግሎት አንድ ለአንድ የግል ድጋፍ ይሰጣል ማመልከቻ ለማስገባት በሁለት ምቹ ስፍራዋች ። ቀጠሮ ለመያዝ ስልክ 703-535-5568 ይደውሉ።**

**ኢንሮል-ቨርጂኒያ (Enroll-Virginia)** በጤና ኢንሹራንስ ገበያ (Health Insurance Marketplace) በኩል ለግለሰቦች እገዛ ይሰጣል። ቀጠሮ ለመያዝ በስልክ ቁጥር 703-647-4748 ይደውሉ።

ስለ ኢንሹራንስ ሽፋን አማራጮች የበለጠ ለማወቅ፣ አዲስ ሽፋንን ለማግኘት ለማመልከት ወይም ያለውን ለማደስ ቤተሰቦች ከ www.coverva.org ወይም ከ www.commonhelp.virginia.gov/access.ማግኘት ይችላሉ። ለልጆቻቸው የጤና ጥበቃ ኢንሹራንስ ማመልከት የሚፈልጉ ስለ ራሳቸው የመኖሪያ ፍቃድም ሆነ በቤታቸው ሳለ አለ ሌላ ግለሰብ መረጃ ማቅረብ አይጠበቅባቸውም።

በACPS ት/ቤት የጤና አማካሪ ቦርድ ለጤና ተደራሽነት አውትሪች ፕሮጀክቱ፣ እና በጄኒፈር ቶልበርት (Jennifer Tolbert)፣ የግዛት ጤና ማሻሻያ ዳይሬክተር ለKaiser Family Foundation የተዘጋጀ

Revised 7/10/2019
Communications Office dnbm

ACPS
Alexandria City Public Schools

# የጤና ጥበቃ አማራጮች

## ለአሌክሳንድርያ ህጻናት

## የሴፍቲ ኔት አቅራቢዎች

ለጤና እንሹራንስ የማይበቁ ህጻናት የሚከተሉትን የሴፍቲ ኔት  አቅራቢዎች መንብኘት ይችላሉ።

### ኔይበርሁድ ሄልዝ

የህጻናት ደህንነት እና የህመም ማታከሚያ ማእከል
703-535-5568

**1200 N. Howard St, Alexandria VA 22304**
የከተማ አውቶብስ  ዳሽ AT2 እና AT1 ይሄዳል።

**2 E. Glebe Road, Alexandria, VA 22305**
በ DASH AT10 እና  AT3  ባስ መግባት ይቻላል

ኔበርሁድ የጤና አገልግሎት ሁሉንም የገቢ መጠን ያለውን ልጆች ያገለግላል የትም ቢኖሩ ወይም ማንኛውም የኤሚግሬሽን ሁኔታ ቢኖራቸውም። እንደቤተሰቡ ገቢ መጠን የሚቀያየር የክፍያ አሰራር ይከተላል። የተወሰኑ ጊዜ የቅዳሜ እና ከስራ በኋላ አገልግሎት ይሰጣል። ለልጆች የሚሰጠው አገልግሎት የሚያካትተው፤ የልጆች ጤንነት እንክብካቤ፣ የታመም ልጆች ህክምና ክትባት፣ የሰውነት ምርመራ፣ የስፖርት የሰውነት ምርመራ ፣ የአእምሮ ምርመራ ፣ እና የጥርስ ህክምና።

### ዌልነስ ኦን ዊልስ የጥርስ ህክምና አውቶቢስ (Wellness on Wheels [WOW] Dental Bus)

703-535-5568

የኤሲፒኤስ ዌልነስ ኦን ሂዊልስ  የጥርስ ህክምና መስጫ አውቶብስ ተንቀሳቃሺ የጥርስ ህክምና ዩኒቲ ሁሉንም የአኤሲፒኢስ ተማሪዋች በጆን አድምስ ፣ በዊሊያም ራምዜ፣ በፐትሪክ ሂንሪ፣ ኮራ ኬሊ ፣ማውንት ቨርነን፣ ጀምስ ፖልክ፣ ሣሙኤል ታከር ፣ በቲሲ ዊሊያም   ት/ቤቶች ያገለግላል።በተንቀሳቃሺ አውቶብስ ውስጥ የምስክር ወረቀት ያላቸው የተሞላ የጥርስ ህክምና እና የተለመዱ የጥርስ ህክምና አሰራሮችን በኔበርሁድ የጤና አገልግሎት የጥርስ ባለሞያዋች ይሰጣል። ይህ  WOW አውቶብስ ሜዲክ አይድ ኢንሺራንስ ፣ ፋሚስ ፣ እና ብዙዋችን የግል ኢንሹራንስ ይቀበላል። ኢንሹራንስ ለሌላቸው ልጆች ክፍያ በገቢ መጠን እና የቤተስብ ብዛት ላይ የተመሰረተ ነው። የተወሰኑ አገልግሎቶች ደግሞ በነፃ ይሰጣሉ።

### የአሌክሳንድርያ ሄልዝ ዲፓርትመንት(AHD) የክሊኒክ አገልግሎት

ብቁነትዎን ለማረጋገጥ እና ቀጠሮ ለማስያዝ በስልክ ቁጥር 703-746-4996 ይደውሉ።

**4480 King Street, Alexandria, VA 22302**
በDASH AT6 ባስ መግባት ይቻላል።

የአሌክሳንድርያ ሄልዝ ዲፓርትመንት(AHD) ለህጻነት ውስን አገልግሎቶች አሉት። ክፍያዎች በቤተሰብ ብዛት እና በገቢ መጠን ሊመሰረቱ ይችላሉ አንድ አንድ አገልግሎቶች ምን አልባትም በነጻ ወይም ያለ ክፍያ ሊሆን ይችላል። የጤና ጥበቃ አገልግሎት ለማግኘት የሚፈልጉ ሰዎች  ስለ መኖሪያ ፍቃዳቸው  መረጃ ለ ለአሌክሳንድርያ ሄልዝ ዲፓርትመንት ማቅረብ አይጠበቅባቸውም።  ስለእያንድንዱ የአሌክሳንድርያ ሄልዝ ዲፓርትመንት(AHD) ክሊንኮች በሚከተለው ዝርዝር መረጃ ቀርቧል።

**ለክትባት አገልግሎት 703-746-4788።** አዲስ ከተወለዱ ህጻናት እስከ ወጣቶች ማንኛውንም ተርታ የክትባት አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ።

**በንጥረ ነገሮች የዳበረ ምግቦች 703-746-4998።** ለአገልግሎቱ የሚበቁ ቤተሰቦች ፣ነብሰጡሮች፣ የሚያጠቡ ፣አዲስ የወለዱ/መጫት እናቶች እና አዲስ የተወለዱ እንዲሁም እድሚያቸው እስከ 5 አመት የሚሆኑ ህጻናት ስለ ንጥረ ነገሮች እና ምግቦች የምክር አገልግሎት እና ምግቦቹን ለመጠቀም ድግሞ ኮፖን ይሰጣል።

### የወጣቶች የጤና ማእከል (The Teen Wellness Center)

703-746-4776 ይደውሉ ወይም “APPT” ወደ 571-329- 2245 3330  የጽሁፍ መልእክት ይላኩ

**3330 King Street, Alexandria, VA 22302**
ነጻ ፓርኪንግ  ለማግኘት በDASH AT5 እና AT6  ባስ

ኣጋርነታችን ከወጣቶች አካላዊ ጤና ማዕከል (Teen Wellness Center) ጋር ሲሆን ይህ ማእከል በ T.C. Williams ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይገኛል። ማዕከሉ የሚመራው ከማኅበረሰብና ሰብአዊ አገልግሎቶች (Department of Community and Health Services) እና ACPS የጤና አገልግሎቶች ጋር በመተባበር በአሌክሳንድሪያ ከተማ የጤና መምሪያ (Alexandria City Health Department) ነው። እድሜቸው ከ12 እስከ 19 የሚደርሱ የአሌክሳንድርያ ኗሪ ወጣቶች ለዚህ ነጻ እና ሚስጥራዊ የጤና አገልግሎት ሊበቁ ይችላሉ። በቨርጂኒያ ህግ መሰረት ጥቂት አገልግሎቶች የቤተሰብ ፍቃድ ይፈልጋሉ። የበወጣቶች የጤና ማእከል የሚከተሉት አገልግሎቶች ይሰጣሉ እነዚህም፡- የአካል የትምህርት ቤት/ ስፖርት፣ አነሰኛ ህመሞች፣ ክትባት፣ የጤና ትምህርት፣ የምክር አገልግሎት፣ የ HIV ምርመራ እና የምክር አገልግሎት፣ የእርግዝና ምርመራ እና ያልተፈለገ እርግዝናን መከላከል፣  የስነ ተዋልዶ ተላላፊ በሽታዎች ምርመራ፣